የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
አዲስ አበባ ነሐሴ ፬ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 53
ADDIS ABABA, 10th August, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፰/፪ሺ፲፰ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ.....ገጽ ፲፱፺፮፬፻፶፱

Content

Proclamation No. 1428/2026

Sharia Courts Proclamation.....Page 19959

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፰/፪ሺ፲፰

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የግል እና የቤተሰብ የሕግ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚነሱ አለመግባባቶችን በፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ በባህላዊና በሃይማኖታዊ ሕጐች ለመዳኘት የሚቻል በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እነዚህን ተቋማት በሌሉ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ እንደሚያቋቁም፣ ቀደም ሲል አገልግሎት ሲሰጡ ለነበሩ ተቋማት ደግሞ እውቅና በመስጠት እንዲያደራጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሀገራችን ተቋቁመው የሚገኙ በመሆኑ፤

PROCLAMATION NO. 1428/2026

FEDERAL SHARIA COURTS PROCLAMATION

WHEREAS, pursuant to Article 34 Sub Article (5) and Article 78 Sub Article (5) of the constitution of the federal democratic republic of Ethiopia, disputes arising in respect of personal and family law matters may, on the basis of the free and voluntary consent of the parties, be adjudicated in accordance with customary and religious laws;

WHEREAS, the constitution of the federal democratic republic of Ethiopia empowers the house of peoples' representatives to establish such institutions where they do not exist and, where such institutions have previously been rendering services, to recognize and organize them accordingly, and, pursuant to such constitutional authority, federal sharia courts have been duly established in the country;

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እንደ አንድ የሀገራችን የፍትሕ አካል የዳኝነት ነጻነታቸው ተጠብቆ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር በመዘርጋት፣ ቀልጣፋና ተደራሽነት ያለው የዳኝነት አገልግሎት መስጠታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለፍርድ ቤቶቹ ዘለቄታዊ እድገትና ጥንካሬ የሚሰራ የፍርድ ቤት አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋምና ፍትሕ ማስፈን የሚያስችል የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋታቸውን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፣

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፹፰/፲፱፺፪ ከጸደቀ ከሩብ ምዕተ ዓመት በላይ ያለፈው በመሆኑና በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ከተከናወኑ ከህግ ማዕቀፍ ለውጦችና ከአሰራር ስርዓቶች ጋር ለማዛመድ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፰/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

WHEREAS, it has become necessary to ensure that the federal sharia courts, as an integral part of the national justice system, exercise their judicial functions with full judicial independence that ensures accountability, and render judicial services that are efficient, effective, and accessible to the public;

WHEREAS, it has become necessary to establish a judicial administration council that promotes the sustainable development and institutional strengthening of the federal sharia courts and creates a judicial administration system that fosters the proper administration of justice;

WHEREAS, more than twenty-five years have lapsed since the enactment of federal sharia courts proclamation no. 188/2000, and in light of the legal, institutional and procedural developments undertaken during that period, it has become necessary to align it with the prevailing legal and administrative framework;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the constitution of the federal democratic republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

PART ONE
General Provisions

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Sharia Courts Proclamation No. 1428/2026".

2. Definitions

In this proclamation, Unless the context requires otherwise:

፩/ "ሕገ መንግስት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ነው፤

1/ **"Constitution"** means the constituton of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፪/ "**የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች**" ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ናቸው፤

2/ **"Federal Sharia Courts**" refers collectively to the Federal Supreme Sharia Court, the Federal High Sharia Court, and the Federal First Instance Sharia Court;

፫/ "ጉባዔ"ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባኤ ነው፤

3/ **"Council"** means the Federal Sharia Courts Administrative Council established under this Proclamation;

፬/ "**የፌደራል ፍርድ ቤቶች የደኅንነት አስተዳደር ጉባኤ**"ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩፺፯፻፴፫/፪፻፲፫ የተቋቋመው ጉባኤ ነው፤

4/ **"Federal Judicial Administration Council"** refers to the Council established under Proclamation No. 1233/2021;

፭/ "**ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት**"ማለት እንደየቅደም ተከተላቸው በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ናቸው፤

5/ **"President and Vice President"** refers the President and Vice President of the Federal each level of the Federa Sharia Courts respectively;

፮/ "**ዳኛ**" ማለት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ተሹሞ የሚሠራ ዳኛ ነው፤

6/ **"Judge"** means a person appointed to serve as a judge at any level of the Sharia Courts;

፯/ "**ተጠሪ ዳኛ**" ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎቶች ኃላፊዎች ሆነው የየምድብ ችሎቶቻቸውን ሥራ የሚመሩ ዳኞች ናቸው፤

7/ **"Representative Judge"** means a judge who is responsible for overseeing the operations of the division courts within the Federal Sharia High Court and the Federal First Instance Sharia Court;

፰/ "**የሥነ ስርዓት ሕጎች**"ማለት በዚህ አዋጅ ስልጣን በተሰጠው አካል የሚዘጋጅ የተጠቃለለ የሸሪዓ ስነ ስርዓት ህጎች መድብል፣ በአሁኑ ወቅት በፍርድ ቤቶቹ በስራ ላይ የሚገኘውን በ፲፱፻፶፭ የወጣው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግና ማሻሻያዎቹን ይጨምራል፤

8/ **"Procedural Laws"** means the consolidated compilation of Sharia Rules of Procedure to be prepared by the body vested with authority under this Proclamation, and includes the currently in force Civil Procedure Code of 1965 and the amendments thereto;

፱/ "**መሰረታዊ የሸሪዓ ሕግ አተረጓጎም ስህተት**" ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሸሪዓ ህግ ስህተት ያለበትና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችል የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ፡-

ሀ) የሸሪዓ ህግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው የሸሪዓ ህግ ምንጭ የሚጠቅስ፤

ለ) በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚችል አንድን ጉዳይ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ በማድረግ የተሰጠ፤

ሐ) በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፤

መ) ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ፤ ወይም

ሠ) ከፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር በመቃረን የተሰጠ፤

የመጨረሻ ውሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ነው፡፡

9/ **"Fundamental Error of Interpretation of Sharia Law"** means a grave error involving rendered in one or more of the following circumstances, which substantially impairs justice and qualifies for review by the Cassation Bench of the Federal Supreme Sharia Court pursuant to Article 6 Sub-Article (3) of this Proclamation in a final judgment, decree, order, or ruling:

a) Misinterprets Sharia law or cites a source of Sharia law that is not applicable to the matter;

b) Rendered by dismissing a matter capable of being adjudicated on the ground that it discloses no cause of action;

c) In respect of which an order has been issued, in the course of execution proceedings, that is not related to the principal judgment;

d) Rendered without the jurisdiction to decide the matter; or

e) Rendered in contravention of the binding interpretation of law given by the Cassation Bench of the Federal Supreme Sharia Court.

፲/ "**የአስተዳደር ሠራተኛ**" ማለት ከዳኛ፣ ረዳት ዳኛ፣ ሬጅስትራርና ሌሎች በጉባዔው በሹመት ከሚመደቡ ሰራተኞችና ኃላፊዎች ውጭ ያሉ ሁሉንም የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እና የጉባዔው ሰራተኞችን ያጠቃልላል፤

10/ **"Administrative Staff"** refers to all employees of the Federal Sharia Courts and the Council, other than judges, assistant judges, registrars, and other employees and officials appointed by the Council;

፲፩/ **"ወቅፍ"** ማለት አንድን ንብረት፣ አገልግሎቱን ወይም ገቢውን በስጦታም ሆነ በውርስ የማይተላለፍ ሆኖ ለበጎ ስራ ይውል ዘንድ መስጠት ነው፤

11/ **"Waqf"** means the giving of a property, its service, or its income for the purpose of being used for charitable work, while making it non-transferable either by gift or by inheritance;

፲፪/ **"ናዚር"** ማለት የወቅፍ ንብረትን ለማስተዳደር፣ ለማልማት፣ በስጦታ እንዳይሰጥና እንዳይለወጥ ለመጠበቅ በወቅፍ አድራጊው ወይም በሸሪዓ የፍትህ አካል ስልጣን በተሰጠው አካል የተሾመ ሰው ነው፤

፲፫/ **"ኒካህ"** ማለት በሸሪዓው ህግ መሰረት የተደረገ የጋብቻ ስምምነት ነው፤

፲፬/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፭/ በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተደነገገው እንደአግባብነቱ የሴትንም ጾታ ያካትታል።

12/ **"Nazir"** means a person appointed by the Waqf founder or by a body empowered under Sharia judicial authority to manage and develop Waqf property and to preserve it from being given as a gift or being altered;

13/ **"Nikah"** means a marriage agreement concluded in accordance with Sharia law.

14/ **"Person"** means a natural person or a person vested with legal personality;

15/ In this Proclamation, references expressed in the masculine gender shall, as appropriate, include the feminine gender.

፫. መቋቋም

፩/ ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፤

፪/ ተጠሪነታቸው ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁመዋል።

3. Establishment

1/ The Federal Supreme Sharia Court, which is accountable to the Federal Supreme Court;

2/ The Federal Sharia High Court and the Federal First Instance Sharia Court, which are accountable to the Federal Supreme Sharia Court, are also hereby established pursuant to this Proclamation.

ክፍል ሁለት

ስለ ፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የወል ዳኝነት ስልጣን

PART TWO

Common Subject Matter Jurisdiction of the Federal Sharia Courts

፬. መሠረቱ

፩/ በፌዴራል መንግስቱ ህጎች በፌዴራል መንግስቱ ስልጣን ስር መሆናቸው በተገለጹ ባለጉዳዮችና ቦታዎች የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከዚህ በታች በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ የወል የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፦

4. Foundation

1/ The Federal Sharia Courts shall have exclusive jurisdiction over the matters listed below where the parties and the subject matter fall under the application of Federal laws:

ሀ) ጥያቄ ያስከተለው ጋብቻ በሸሪዓ ህግ መሰረት የተፈጸመ የሆነ እንደሆነ ወይም ባለጉዳዮቹ በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ፈቅደው ከሆነ፤ ማናቸውም የጋብቻና የጋብቻ ውጤት፡ የፍቺና የፍቺ ውጤት፡ የቀለብ አወሳሰን፡ አካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት አስተዳደግና ሞግዚትነት ወይም በቤተሰብ ተዛምዶ እንዲሁም የህግ ችሎታ ያጡ ሰዎች ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን አስመልክቶ፤

a) Where the cause of action arises from a marriage conducted under Sharia law or where the parties consent to be adjudicated under Islamic religious law, matters related to any issues related to marriage and its consequences, divorce and its consequences, child custody and guardianship of minors, family-related matters, and issues involving persons lacking legal capacity, shall fall under the jurisdiction of the Federal Sharia Courts;

ለ) የወቅፍና የወቅፍ አስተዳደር (ናዚርነት)፣ የስጦታ (ሂባ)፣ የውርስ፣ ውርስ ማጣራትና ውርስ ሀብት ክፍፍል፣ ወይም የኑዛዜ ጉዳዮችን በተመለከተ፤

b) With respect to matters relating to Waqf and the administration of Waqf (Nazirship), gifts (Hiba), inheritance, the ascertainment of inheritance, and the distribution of inherited property, or testamentary matters;

ሐ) በግልጽ የሸሪዓ ህጉን መሰረት አድርገው የተመሰረቱ ስምምነቶችና ግንኙነቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች፤

c) Disputes arising from agreements and relations clearly established on the basis of sharia law;

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል-ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) በተገለጹት ጉዳዮች ላይ በሚቀርቡ ክሶች ጋር ተያይዞ የሚሰጡ ፍርዶችና ውሳኔዎች አፈጻጸምና ወጪና ኪሣራ መወሰንን በተመለከተ፤

d) All matters related to judgments and decisions made in relation to cases covered under this Article Sub-Article (1) paragraphs (a) through (c), including enforcement, assessment of costs, and determination of damages;

ሠ) በውጪ ሀገር የሞተ ወይም የሞተች ሙስሊም ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያዊት የቀብር ስነ ስርዓት እንዲፈጸም የሚሰጥ ፍቃድንና የጋብቻ ስነ ስርዓትን የሚያከናውኑ የሸሪዓ አጋቢዎች ፍቃድ መስጠትና መሻር፤

e) Issuance of permits for burial rites of Ethiopian Muslims who died abroad, and authorization and approval of officiants conducting Sharia-based marriage ceremonies;

(ረ) በመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ የፍቺ ውሳኔን መሰረት በማድረግ ኒካህ እንዲወርድ ማድረግ አለበት።

f) Pronouncing the termination of the Nikah on the basis of a divorce decision rendered by a regular court.

፪/ በዚህ አንቀጽ ስር በተገለፁት ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤቶቹ የዳኝነት ሥልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፍቃደኝነታቸው ከዚህ በታች በአንቀጽ ፭ በተደነገገው መሰረት የተረጋገጠ ከሆነ ብቻ ይሆናል።

፭. <u>ስለ ፍቃደኝነት አሰጣጥ ወይም አገላለጽ</u>

፩/ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ተከራካሪዎች በፍርድ ቤቶቹ ለመዳኘት ፍቃደኝነት ተገኝቷል የሚባለው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ የወል የዳኝነት ስልጣን በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት አቤቱታ አቅርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኑን በችሎት በቀረበበት የመጀመሪያ ጊዜ በግልጽ ያሳሳወቀ እንደሆነ ነው።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ የደረሰው ተከራካሪ ወገን ባለመቅረቡ በስነ ስርዓት ህጉ መሰረት ጉዳዩ ተከራካሪ ወገን በሌለበት እንዲቀጥል የተወሰነ እንደሆነ ፈቃድ እንደተገኘ ተደርጎ ይቆጠራል።

፫/ ግንኙነቱ በተመሰረተበት ውል ወይም ማንኛውም ስምምነት ላይ ግራ ቀኙ ከውሉ ወይም ከስምምነቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶች በሸሪዓ ህጉ ወይም በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ እንደሚዳኙ በግልጽ ያስቀመጡ እንደሆነና ጉዳዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ስር የሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው ጉዳይ ከሆነ በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ እንዲታይ ፍቃድ እንደተገኘ ይቆጠራል።

2/ The jurisdiction of the Federal Sharia Courts over the above matters shall be valid only when the consent of the parties to be adjudicated under Islamic law is confirmed based on the procedure outlined under Article 5 of this proclamation.

5. <u>Meaning of Consent and Objection Procedure</u>

1/ Consent by parties to be adjudicated by the Sharia Courts shall be deemed to have been given where one party brings a case before the Sharia Court on matters within its jurisdiction, and the other party does not explicitly object to the jurisdiction of the court by stating that they are unwilling to be adjudicated by the court at the first hearing.

2/ Without prejudice to the provision set out under Sub-Article (1) of this Article, where a matter is ordered to proceed in the absence of a party who, having been duly served with the Court's summons, failed to appear, in accordance with the Rules of Procedure, such party shall be deemed to have given consent.

3/ Where, in the contract or any agreement upon which the relationship is established, the parties have expressly provided that disputes arising in connection with the contract or agreement shall be adjudicated in accordance with Sharia law or by the Sharia Court, and where the matter is one over which the Sharia Court is granted jurisdiction under Article 4 of this Proclamation, consent shall be deemed to have been obtained for the matter to be heard by the Sharia Court.

፬/ በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ተከራካሪ ከሆኑ ወገኖች መብት የመነጨለት ተተኪ ባለጉዳይ በመታየት ላይ ባለው ጉዳይ ላይ ፍቃደኝነትን መሰረት አድርጎ መቃወሚያ ለማንሳት አይችልም፡፡

4/ A successor-in-interest deriving rights from a party to proceedings before the Sharia Court shall not be entitled to raise an objection, in respect of the pending matter, on the ground of consent.

፭/ የሶስተኛ ወገን ተከራካሪዎችን ፍቃደኝነት በሚመለከት፡-

5/ Regarding the consent of third-party participants:

ሀ) በሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይቶ በተወሰነ ወይም በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ የተሰጠው ወይም ሊሰጥ የሚችለው ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መብትና ጥቅሜን ይነካል የሚል ወገን በስነ ስርዓት ህጉ መሰረት በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፍቃደኛ አለመሆኑንም በግልጽ እስካላመለከተ ድረስ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ መብትና ጥቅሙ የሚነካ መሆኑን አረጋግጦ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ከወሰነ በኋላ፤

a) A third party whose application to set aside a judgment or order of to intervene in a suit being adjudicated in the federal sharia courts has been allowed, on the grounds that their right or interest is or may be affected by a judgment or order rendered or to be rendered in the case and the said third party fails to clearly state their objection to the Court's jurisdiction in their application to set aside or intervene;

ለ) በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የታዘዘ ሶስተኛ ወገን ለክርክሩ በሚያቀርበው አቤቱታ ጽሁፍ፣ መከራከሪያ ጽሁፍ ወይም ማመልከቻ ላይ በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፍቃደኛ አለመሆኑንም በግልጽ እስካላመለከተ ድረስ፤

b) A third party ordered to join a proceeding before the sharia court, who does not explicitly object to the Court's jurisdiction in their statement of defense;

ፍቃደኝነትን መሰረት አድርጎ መቃወሚያ ለማንሳት አይችልም፡፡

may not raise an objection on grounds of consent later on.

፮/ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደሌለው በመግለጽ መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎቹን ያሠናብታል፡፡

6/ Where it is established that there is no consent to be adjudicated by the Sharia Court, the Court shall declare that it lacks jurisdiction to hear the matter, close the case file, and dismiss the parties.

ክፍል ሶስት

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን

፮. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣንና የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ውጤት

፩/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ) ከአንድ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎት ወደ ሌላ የፌደራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲዘዋወር በሚቀርብ ጥያቄ ላይ፤ እና

ለ) በክልልና በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ወይም በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች መካከል የሚነሳ የዳኝነት ስልጣን በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ።

፪/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ) የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች፤ ወይም

ለ) የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮችን።

PART THREE

Functional Jurisdiction of Federal Sharia Courts

6. Jurisdiction of the Federal Supreme Sharia Court and Decisions of the Cassation Bench

1/ The Federal Supreme Sharia Court shall have first instance jurisdiction over the following matters:

a) Applications for the transfer of a case from one Bench of the Federal High Sharia Court to another Bench of the Federal High Sharia Court; and

b) Applications relating to disputes concerning jurisdiction arising between Regional Sharia Courts and Federal Sharia Courts, or among the Federal Sharia Courts.

2/ The Federal Supreme Sharia Court shall have appellate jurisdiction over the following matters:

a) Matters in which the Federal High Sharia Court has rendered a decision in the exercise of its first instance jurisdiction; or

b) Matters in which the Federal High Sharia Court, in the exercise of its appellate jurisdiction, has rendered a decision different from that rendered by the Federal First Instance Sharia Court.

፫/ በተጨማሪም የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ሲሆን ችሎቱም፡-

ሀ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ዓይቶ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ወይም የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ አይቶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ፤

ለ) የክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ስልጣን ያለው ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ፤ ወይም

ሐ) የሸሪዓ ህግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው የሸሪዓ ህግ ምንጭ የሚጠቅስና በሀገር ደረጃ ወጥ የሆነ የሸሪዓ ህግ አተረጓጎም እንዲኖር የሚረዱ ጉዳዮች ላይ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የሸሪዓ ህግ ትርጉም ጋር ተቃርኖ የተወሰነ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ፤

የተፈጸመ መሰረታዊ የሸሪዓ ህግም ሆነ ወይም የስነ ስርዓት ህጎች አተረጓጎም ስህተት አለበት ተብሎ ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል።

3/ Furthermore, a Cassation Bench of the Federal Supreme Sharia Court is hereby established under this Proclamation, and the Bench shall have the power to examine and determine petitions submitted by the parties alleging that a fundamental error in the interpretation of substantive Sharia law or the Rules of Procedure has been committed in relation to:

a) A final decision rendered by the Federal Supreme Sharia Court in the exercise of its appellate jurisdiction, or a final decision rendered by the Federal High Sharia Court in the exercise of its appellate jurisdiction affirming the decision of the lower court;

b) A final decision rendered by the Sharia Court having final jurisdiction within a Regional Supreme Sharia Court; or

c) A final decision that misinterprets Sharia law, cites a source of Sharia law that is not applicable to the matter, concerns issues that would contribute to ensuring the uniform interpretation of Sharia law at the national level, or is rendered contrary to the binding interpretation of Sharia law issued by the Cassation Bench of the Federal Supreme Court or the Cassation Bench of the Federal Supreme Sharia Court.

፬/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየመበት የሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው መሰረታዊ የሸሪዓ ህግ ወይም የስነ ስርዓት ህጎች ትርጉም በሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይተው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻው ውሳኔ ሲሆን ውሳኔው ከተሰጠበት እለት አንስቶ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የሀገሪቱ የፌዴራልም ሆነ የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

4/ An interpretation of substantive Sharia law or procedural laws rendered by the Cassation Division of the Federal Supreme Sharia Court, sitting with not fewer than five judges, shall be binding on Federal and Regional Sharia Courts at all levels from the date the decision is rendered.

፭/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎቶች አስገዳጅ ህግ ትርጉም የተሰጠባቸው ውሳኔዎች በኤሌክትሮኒክስ ወይም በህትመት ሚዲያዎች በተቻለ ፍጥነት ያሰራጫል፡፡

5/ The Federal Supreme Sharia Court shall, as promptly as practicable, publish and disseminate, through electronic or print media, the decisions of its Cassation Benches that contain binding interpretations of the law.

፮/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተደራጅቶ ወደ ስራ እስከሚገባበት ጊዜ ድረስ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በባለጉዳዮች ጠያቂነት በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ችሎቶች መካከል መሰረታዊ የትርጉም ልዩነት ያለባቸው የሸሪዓውን ህግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲነሱ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው እንዲያዩት ለማድረግ ይችላል፡፡

6/ Pending the organization and commencement of operations of the Cassation Division of the Federal Supreme Sharia Court, the President of the Federal Supreme Sharia Court may, upon the application of the parties, direct that cases involving fundamental inconsistencies in the interpretation of Sharia law among the divisions of the Federal Sharia Courts be heard by a bench consisting of not fewer than five judges.

፯/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሰጡት የመጨረሻ ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ላይ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አተረጓጎም መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞብኛል በሚል ተከራካሪ ወገን አመልካችነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አይቶ ተፈጸመ በተባለው የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ህግ ግድፈት ላይ ብቻ ተገቢውን የመወሰን ስልጣን አለው፡፡

7/Where a party alleges that a fundamental error in the interpretation of the Civil Procedure Code has been committed in a final order, ruling, judgment, or decision rendered by a Federal Sharia Court, the Cassation Bench of the Federal Supreme Court shall, upon the application of such party, have jurisdiction to examine the matter and determine only the alleged error in the interpretation of the Civil Procedure Code.

፯. <u>የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ስልጣን</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖሩታል፡-

፩/ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግምታቸው ከብር ፲ ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን ብር) በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

፪/ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፫/ አንድን ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎት ወደ ሌላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር የሚቀርብን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፰. <u>የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን</u>

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግምታቸው እስከ ብር ፲ ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን ብር) የሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ወይም ግምታቸው በገንዘብ ሊተመን በማይችሉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

7. <u>Jurisdiction of the Federal Sharia High Court</u>

The Federal Sharia High Court shall have the following powers and jurisdiction:

1/ The Federal High Sharia Court shall have first instance jurisdiction over matters the value of which exceeds Birr 10,000,000 (Ten Million Birr).

2/ The Federal High Sharia Court shall have appellate jurisdiction to hear appeals from decisions rendered by the Federal First Instance Sharia Court.

3/ The Federal High Sharia Court shall have jurisdiction to hear applications for the transfer of a case from one Bench of the Federal First Instance Sharia Court to another Bench of the Federal First Instance Sharia Court, or to itself.

8. <u>Jurisdiction of the Federal First Instance Sharia Court</u>

The Federal First Instance Sharia Court shall have first instance jurisdiction over matters the amount or value of which does not exceed Birr 10,000,000 (Ten Million Birr), as well as over matters whose value cannot be assessed in monetary terms.

ክፍል አራት

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሰራር

፱. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች፣ ዳኞችና ሌሎች ሰራተኞች

፩/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዝዳንት እና አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞችና ሬጅስትራሮች ይኖሩታል።

፪/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።

፲. የፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች

የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለየፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንት፣ በየፍርድ ቤቶቹ ያለው የስራ ስፋትና ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ተጠሪ ዳኞች፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች፣ ሬጅስትራሮች እንዲሁም ሌሎች ሠራተኞች ይኖሯቸዋል።

፲፩. ስለ ውክልና እና ማስቻያ ስፍራ

፩/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአንድ ዳኛ ያስችላሉ።

፪/ በፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎቶች አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ተሰይመው ያስችላሉ።

፫/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ማስቻያ ስፍራ አዲስ አበባ ይሆናል ።

PART FOUR

Structure and Operations of Federal Sharia Courts

9. Presidents, Judges, and Other Staff of the Federal Supreme Sharia Court

1/ The Federal Supreme Sharia Court shall have one President and one Vice President, as well as the judges and registrars necessary for its operations.

2/ The Federal Supreme Sharia Court shall also have other necessary staff for the execution of its duties.

10. Federal High and First Instance Sharia Courts

The Federal High Sharia Court and the Federal First Instance Sharia Court shall each have a President, and, where the workload and circumstances of the respective Court so require, a Vice-President, supervising judges, such number of judges as may be necessary for the proper discharge of the Court's functions, registrars, and such other employees as may be necessary.

11. Benches of the Federal Sharia Courts, their Organization and Deligation

1/ Benches in the Federal First Instance Sharia Court shall be presided over by a single judge.

2/ Benches in the Federal Sharia High Court and the Federal Supreme Sharia Court shall be composed of one presiding judge and two associate judges.

3/ The seat of the Federal Supreme Sharia Court shall be in Addis Ababa.

፬/ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የማስቻያ ስፍራ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ይሆናል።

፭/ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የተገልጋዩን ማህበረሰብ ብዛት እና የፍርድ ቤቶቹን በጀት ባማከለ ሁኔታ ተጨማሪ ምድብ ችሎቶች ይኖሯቸዋል።

፮/ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ስፍራዎች ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ በተጨማሪ በክልሎችም ሊደራጁ የሚችሉ ሲሆን፣ ባልተደራጁባቸው ክልሎች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ስልጣን ለክልል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች፣ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ስልጣን ለክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በውክልና ተሰጥቷል።

፲፪. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ የፌዴራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ ይሆናል።

፪/ የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ለማይችል ባለጉዳይ ፍርድ ቤቱ አስተርጓሚ ይመድብለታል።

፫/ የምልክት ቋንቋ ለሚጠቀም አካል ጉዳተኛ ተገልጋይ እና ሰራተኛ፤ ብሬይልና ረዳት ለሚያስፈልጋቸው ዳኞችና ሰራተኞች ባለሙያ በፍርድ ቤቱ ይመደብላቸዋል።

4/ The seats of the Federal High and First Instance Sharia Courts shall be in Addis Ababa and in Dire Dawa city administrations.

5/ The Federal High Sharia Court and the Federal First Instance Sharia Court may establish such additional Divisional Benches as may be required, taking into account the size of the population served and the budgetary capacity of the respective Courts.

6/ The Federal First Instance and High Courts of Sharia may, in addition to Addis Ababa and Dire Dawa, establish seats in the Regional States, In Regional States where such Courts have not been established, the jurisdiction of the Federal First Instance Sharia Court is delegated to the Regional High Sharia Courts, and the jurisdiction of the Federal High Sharia Court is delegated to the Regional Supreme Sharia Courts.

12. Working Language of the Federal Sharia Courts

1/ The official languages of the Federal Sharia Courts shall be the official working language of the Federal government.

2/ The court shall assign an interpreter for any party who cannot speak the working language of the Federal government.

3/ The Court shall assign qualified sign language interpreters for parties and employees with hearing impairments, and Braille and other assistive professionals for judges and employees who require them.

፲፫. በግልጽ ችሎት ስለማስቻል

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማስቻል አለባቸው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም የተከራካሪዎችን የግል ህይወት፣ የህዝብ ሞራል ሁኔታ ወይም ግብረገብነትን ለመጠበቅ በሸሪዓ ህጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቶቹ በዝግ ችሎት ማስቻል አለባቸው።

13. Open Court Proceedings

1/ Federal Sharia Court hearings shall be conducted publicly.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, where it is necessary under Sharia law to protect personal privacy, public morals, or public order, the court shall hold a closed session.

፲፬. ከችሎት ስለመነሳት

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል።

፪/ ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ የሚነሳበትን ምክንያትና ሁኔታ እንዲሁም ማመልከቻው ስለሚያስከትለው ኪሳራና ቅጣት በተመለከተ ተፈጻሚነት ያላቸው የሸሪዓ ህጎች እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ላይ ከሸሪዓ ህጉ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ አግባብነት ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፫/ ከላይ የተመለከቱት የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዳኛው በችሎት ላይ ሊቀመጥ የማይገባው መሆኑን በራሱ ሲያውቅ ከችሎት ተነስቶ ሌላ ዳኛ እንዲተካ ይደረጋል።

14. Withdrawal of Judges

1/ A party to a case may submit a request to the court for the withdrawal of a federal sharia court judge from a case.

2/ Without prejudice to the applicable rules of Sharia governing the grounds and circumstances for the recusal of a judge against whom an application for recusal has been filed, and the consequences, costs, and sanctions arising from such application, the relevant provisions of the Federal Courts Proclamation shall apply to the extent that they are not inconsistent with Sharia law.

3/ Without prejudice to the above provisions, where a judge becomes aware that he ought not adjudicate a particular matter, he shall recuse himself and another judge shall be assigned to hear the case.

ክፍል አምስት

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች መስፈርትና አሿሿም

፲፭. ዳኛ ሆኖ ለመመረጥ የሚያበቁ መስፈርቶች

፩/ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሙስሊም ኢትዮጵያዊ በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል፡-

ሀ) በእስልምና ትምህርት ተቋማት በሸሪዓ ሕግ የሠለጠነ ወይም በሸሪዓ ሕግ በቂ የሆነ ልምድና ዕውቀት ያካበተ፤

ለ) በታታሪነቱና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤

ሐ) የወንጀል ሪኮርድ የሌለበት ወይም ከዚህ በፊት ከየትኛውም ተቋም በስነምግባር ጉድለት ያልተሰናበተ፤

መ) የየትኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፤

ሠ) ዳኛ ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ፤ እና

ረ) ዕድሜው ከ፳፭ ዓመት በላይ የሆነ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ለፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ወይም ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚወዳደር ዳኛ በሸሪዓ ፍርድ ቤት በዳኝነት ያገለገለበት እንደ ልዩ መመዘኛ ይያዝለታል ፡፡

፫/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኝነት መስፈርቶችና የምልመላና አመራረጥ አሰራርን የሚደነግግ መመሪያ ያወጣል፡፡

PART FIVE

Criteria and Appointment of Federal Sharia Court Judges

15. Eligibility for Appointment as a Judge

1/ Any Ethiopian Muslim who fulfills the following criteria may be appointed as a judge of the Federal Sharia Courts:

a) Has studied Sharia law at recognized Islamic institutions or has sufficient experience and knowledge in Sharia law;

b) Has a good reputation in conduct and character;

c) Has no criminal record and has not been dismissed from any previous employment for ethical misconduct;

d) Is not a member of any political party;

e) Is willing to serve as a judge; and

f) Is over the age of 25.

2/ Subject to Sub-Article (1) of this Article, prior service as a judge of a Sharia Court shall be taken into account as a special qualification in evaluating the suitability of a candidate for appointment as a judge of the Federal High Sharia Court or the Federal Supreme Sharia Court.

3/ The administration council of the Federal Sharia Courts shall, in consultation with the Ulama Council of Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council, issue Directive detailing the qualifications, nomination, and selection process for Sharia Court judges.

፲፮. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች እና ዳኞች አሿሿም

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የዳኞችን ምልመላ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ድንጋጌዎች መሰረት ያከናውናል፡፡

፪/ ጉባዔው የተመለመሉትን ዕጩ ዳኞችን አጭር የሕይወት ታሪክ መግለጫ አዘጋጅቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት በማቅረብ ሹመታቸው እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

፫/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሮዝዳንቶች እና ዳኞች ሹመት የሚጸድቀው፡-

ሀ) በሶስቱም ደረጃ የሚገኙ የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ሹመት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን፣

ለ) በየትኛውም ደረጃ የሚመደቡ ዳኞች ሹመት በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡

፲፯. ስለ ዳኞች ደሞዝ፣ ጥቅማጥቅምና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች

በዚህ አዋጅ መሰረት ለተሾመ ማንኛውም ዳኛ የፌዴራል ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ አዋጅ ስለ ዳኞች የስራ ዘመን፣ ያለመከሰስ መብት፣ የደረጃ እድገት፣ ዝውውር፣ እረፍት፣ የምርምር ስራ ተሳትፎ፣ ስልጠና፣ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ የስራ ስንብትና ሌሎችም ጉዳዮች የተደነገጉ ድንጋጌዎች በሙሉ ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞችም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

16. Appointment of Presidents and Judges of the Federal Sharia Courts.

1/ The Federal Sharia Courts Administration Council shall, in collaboration with the Ulama Council of the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council, conduct the recruitment of judges in accordance with the provisions of Article 15 of this Proclamation.

2/ The Council shall prepare and submit the short-listed candidate judges along with their brief biographical information, based on Sub-Article (3) of this Article, for the confirmation of their appointments.

3/ The appointment of Presidents and judges of the Federal Sharia Courts shall be confirmed as follows:

a) The Presidents and Vice-Presidents of the Federal Sharia Courts at all three levels shall be appointed by the House of Peoples' Representatives of the FDRE upon the nomination of the President of the Federal Supreme Court;

b) Judges appointed at any level shall be appointed by the House of Peoples' Representatives of the FDRE upon the nomination of the President of the Federal Supreme Sharia Court.

17. Remuneration, Benefits and Other Related Matters of Judges

The provisions of the Federal Judicial Administration Council Proclamation concerning the tenure, immunity, promotion, transfer, leave, participation in research, training, V.I.P services, benefits, retirement, and other related matters of judges shall be fully applicable to judges of Federal Sharia Courts appointed under this Proclamation.

ክፍል ስድስት

ስለ ፕሬዝዳንቶች፣ ምክትል ፕሬዝዳንትና ተጠሪ ዳኞች አሿሿም፣ ስልጣንና ተግባር

፲፰. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በፍርድ ቤቱ አስተዳደር ጉባዔ እና በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ትብብር ተመልምለው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ አንድ ፕሬዝዳንትና አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት ይኖሩታል፡፡

፪/ የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ እና በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ትብብር የሚመለመሉና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሰየሙ አንድ፣ አንድ ፕሬዝዳንት ይኖራቸዋል፡፡

፫/ ከምድብ ችሎቶችና የፍርድ ቤቶቹ ስራ ብዛት አንጻር እንደ አስፈላጊነቱ ለፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ምክትል ፕሬዝዳንቶችና የምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኞች ሊኖሯቸው ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የሚሾሙ ምክትል ፕሬዝዳንቶች በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ እና በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ትብብር ተመልምለው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት የሚሾሙ ሲሆን፣

PART SIX

Powers and Responsibilities Regarding the Appointment of Presidents, Vice Presidents, and Representative Judges

18. General Provisions

1/ The Federal Supreme Sharia Court shall have a President and a Vice-President, who shall be recruited by collaboration of the Courts' Administration Council and the Ulama Council of the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council, and appointed by the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia upon the nomination of the President of the Federal Supreme Court.

2/ The Federal High and First Instance Courts of Sharia shall each have a President, who shall be recruited by the Courts' Administration Council in collaboration with the Ulama Council of the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council and appointed by the House of Peoples' Representatives of the FDRE upon the nomination of the President of the Federal Supreme Court.

3/ Depending on the structure and workload of the divisions and courts, Vice Presidents and Representative Judges may be appointed to the Federal High and First Instance Sharia Courts.

4/ Vice-Presidents appointed pursuant to Sub-Article (3) of this Article shall be recruited by the Courts' Administration Council in collaboration with the Ulama Council of the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council and appointed by the House of Peoples' Representatives upon the nomination of the President of the Federal Supreme Court;

የምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኞች በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በጉባዔው የሚሾሙ ይሆናል።

፭/ በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ከጉባዔው ፩/፫ኛ በሚሆኑት አባላት ጥያቄ በ፪/፫ኛ ድምጽ ተወስኖ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ በማንኛውም ጊዜ ከኃላፊነታቸው ይነሳሉ።

5/ The Presidents and Vice-Presidents of the Federal Sharia Courts at all levels may be removed from office at any time upon a resolution adopted by a two-thirds majority vote of the members of the Courts' Administration Council, following a motion initiated by not less than one-third of its members, and upon approval by the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic.

፲፱. <u>የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባር</u>

19. <u>Powers and Duties of the President of the Federal Supreme Sharia Court</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፡-

The President of the Federal Supreme Sharia Court:

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን በበላይነት ያስተዳድራል፤

1/ Shall oversee the administration of all Federal Sharia Courts;

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዝዳንቱ፡-

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the President shall:

ሀ) በየደረጃው ያሉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን መዋቅር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድለት በሥራ ላይ ያውላል፤

a) Prepare the organizational structure of Sharia Courts at all levels and submit same to the Federal Sharia Courts Administrative Council; and implement same upon approval;

ለ) በዚህ አዋጅ ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ የተሰጡ ስልጣንና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ዳኞችን፣ የፌዴራል ጠቅላይና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሰብሳቢ ዳኞች፣ ለፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ዳኞችን እንዲሁም ሌሎች ተሿሚዎችን በየደረጃው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውስጥ በመደልደል ያሠራል፤

b) Without prejudice to the powers and duties vested in the Federal Sharia Courts Administrative Council under this Proclamation, assign and manage judges, presiding judges of the Federal Supreme and High Sharia Courts, representative judges of the Federal High and First Instance Sharia Courts, as well as other appointees within the various levels of the Federal Sharia Courts;

ሐ) የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ደልድሎ ያሰራል፣ ያሰናብታል፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24ንዑስ አንቀጽ (12) መሰረት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች ቀጣይነት ያለው ስልጠና ማግኘታቸውን ይከታተላል፤

ሠ) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ሰራተኞችን የሚመለከቱ ህጎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24ንዑስ አንቀጽ (8) መሰረት የተደነገጉ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰራተኞች የአሰራር ስነ ስርዓቶችን ተፈጻሚ መሆናቸው ይከታተላል፤

ረ) የፍርድ ቤቶቹንና የጉባዔውን የስራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እቅድና በጀት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመቅረቡ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት በማቅረብ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲፈቀድለት በሥራ ላይ ያውላል፤

ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ መሰረት ለፍርድ ቤቱ በመንግስት ከሚገኘው በጀት በተጨማሪ ለፍርድ ቤቶቹ የሚያስፈልጋቸውን የበጀት ድጋፍ ከጉባዔው ጋር በመተባበር ያፈላልጋል ጉባዔው ድጋፉን ለመቀበል ፈቅዶ ሲያጸድቅለትም ስራ ላይ ያውላል፤

ሸ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤትን ፋይናንስ ያስተዳድራል፤

ቀ) የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስላከናወኗቸው ስራዎች አፈፃፀም በቋሚነት በየሩብ ዓመቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤

c) Employ, assign, and dismiss the administrative staff of the Federal Sharia Courts;

d) Ensure that Sharia Court judges receive continuous training in accordance with Article 24 Sub-Article (12) of this Proclamation;

e) Oversee the implementation of laws governing Federal Courts' administrative staff, as well as the rules of procedure for Federal Sharia Court staff enacted pursuant to Article 24(8) of this Proclamation;

f) Prepare the work plan and budget of the Courts and the Council; submit the same to the President of the Federal Supreme Court fifteen days prior to the submission of the Federal Courts' plan and budget to the House of Peoples' Representatives of the FDRE, and implement the same upon approval;

g) Pursuant to Article 33 of this Proclamation, seek additional budgetary support required for the courts in collaboration with the Council, and utilize such support upon the Council's approval;

h) Administer the finances of the Federal Supreme Sharia Court;

i) Submit quarterly performance reports of the Federal Sharia Courts to the President of the Federal Supreme Court;

በ) የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን እና የጉባዔውን የስራ አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀም ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ከማቅረቡ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ያቀርባል፤

ተ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤትን በመወከል አስፈላጊ ቦታዎች ላይ ይገኛል፤ መግለጫዎችን ይሰጣል፤

ቸ) ሌሎችም በዚህ አዋጅ የተሰጡትንና ከፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ የሚሰጡትን ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

j) Submit the annual performance and budget utilization report of the Federal Sharia Courts and the Council fifteen days prior to the submission of the annual performance report of the Federal Courts by the President of the Federal Supreme Court;

k) Represent the Federal Supreme Sharia Court in official functions and issue statements;

l) Perform such other legal functions as are provided for in this Proclamation or assigned by the Federal Sharia Courts Administrative Council.

፳. <u>የምክትል ፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ፕሬዝዳንቱ፡

፩/ በፕሬዝዳንቱ የሚመሩለትን ጉዳዮች ያከናውናል።

፪/ ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱን ተክቶ ይሠራል።

20. <u>Powers and Functions of the Vice-President</u>

The Vice President shall:

1/ Execute the matters assigned to him by the President.

2/ Act on behalf of the President in the latter's absence.

፳፩. <u>የፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች ስልጣንና ተግባር</u>

የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች፡-

፩/ ፍርድ ቤቶቻቸውን ይወክላሉ።

፪/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የየፍርድ ቤቶቻቸውን ሥራ ይመራሉ።

፫/ የየፍርድ ቤቶቻቸውን ፋይናንስ ያስተዳድራሉ።

፬/ የየፍርድ ቤቶቻቸውን የአስተዳደር ሠራተኞች ያስተዳድራሉ።

21. <u>Powers and Functions of the Presidents of the Federal High and First Instance Sharia Courts</u>

The Presidents of the Federal High and First Instance Sharia Courts shall:

1/ Represent their respective courts.

2/ Direct the operations of their respective courts in accordance with Directives issued by the President of the Federal Supreme Sharia Court.

3/ Administer the finances of their respective courts.

4/ Manage the administrative staff of their respective courts.

ሯ/ ስለተከናወኑ ሥራዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በስታትስቲክስ የተደገፈ መግለጫ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

ሷ/ ስለ ሥራዎቻቸው እንደአስፈላጊነቱ ከጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ጋር በመመካከር ያከናውናሉ፡፡

ሿ/ ሌሎችም በሕግና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የሚሰጧቸውን ህጋዊ ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

ክፍል ሰባት
የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ

፳፪. መቋቋም

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ) ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ጉባዔው የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ነው፡፡

፳፫. ስለጉባዔው አደረጃጀት

፩/ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፤

ለ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፤

ሐ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት፤

መ) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንድ ተወካይ፤

ሠ) በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞች የጋራ ስብሰባ የሚወከል አንድ የዳኞች ተወካይ፤

5/ Submit quarterly reports, supported by statistics, to the President of the Federal Supreme Sharia Court regarding the activities carried out.

6/ As necessary, coordinate with the President of the Federal Supreme Sharia Court regarding their activities.

7/ Perform other functions assigned to them by law.

PART SEVEN
Federal Sharia Courts Administrative Council

22. Establishment

1/ The Federal Sharia Courts Administration Council (hereinafter referred to as the "Council") is hereby established under this Proclamation and shall be accountable to the Federal Supreme Court.

2/ The Council shall have its own legal personality.

23. Composition of the Council

1/ The Council shall have the following members:

a) The President of the Federal Supreme Court;

b) The President of the Federal Supreme Sharia Court;

c) The Vice-President of the Federal Supreme Sharia Court;

d) A representative from the House of Peoples' Representatives of the FDRE;

e) A representative of judges elected by the general assembly of Federal Sharia Court judges;

ረ) ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ አባላት ውስጥ ሁለት ተወካይ፤

ሰ) በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የሚወከል በዳኝነት ስራ የረዥም ጊዜ ልምድ ያለው ሙስሊም የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛ፤

ሸ) በሞያዊ ብቃት፣ በስነ ምግባሩ የተመሰገነና ማህበራዊ ተቀባይነቱ ከፍ ያለ፣ ለህግ የበላይነትና ለሸሪዓ ፍትህ ስርዓቱ እድገት ቁርጠኝነት ያለውና የጎላ አስተዋጽዖ ያበረከተ ወይም ለማበርከት ይችላል ተብሎ የሚገመት በጉባዔው የሚመረጥ አንድ ሰው።

፪/ ከጉባኤው አባላት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ተወካይ ሴት መሆን ይኖርበታል።

፫/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እንደ ቅደም ተከተላቸው የጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይሆናሉ።

፬/ የጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በሌሉበት ጊዜ ጉባዔው ከአባላቱ መካከል በድምጽ ብልጫ አንድ ጊዚያዊ ሰብሳቢ በመሰየም ስራውን ያከናውናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከፊደልተራ (መ) እስከ (ሸ) ድረስ የተመለከቱት የጉባዔው አባላት ከጉባዔው አባልነታቸው ለመልቀቅ በሚፈልጉበት ወቅት በጉባዔው ጽሕፈት ቤት በኩል ቢያንስ ከሁለት ወር አስቀድሞ ለጉባዔው በጽሁፍ መልቀቂያ ማቅረብ አለባቸው።

f) Two representatives from the Council of Ulamas of the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council;

g) A Muslim Federal Court judge with extensive judicial experience, to be represented by the President of the Federal Supreme Court;

h) A person elected by the Council who is distinguished for professional competence and integrity, enjoys high social standing, and has demonstrated or is expected to contribute significantly to the rule of law and the development of the Sharia justice system.

2/ The membership of the Council shall include not fewer than two women.

3/ The President of the Federal Supreme Court and the President of the Federal Supreme Sharia Court shall be the Chairperson and Vice-Chairperson of the Council, respectively.

4/ In the absence of both the Chairperson and the Vice-Chairperson, the Council shall perform its duties by electing a temporary chairperson from among its members by a majority vote.

5/ Members of the Council referred to in Sub-Article (1) paragraph (d) to (h) of this Article, who wish to resign from their membership, shall submit a written resignation to the Council through its Secretariat at least two months in advance.

፳፬. የጉባዔው ስልጣንና ተግባር

ጉባዔው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንትነት የተመለመሉ እጩዎችን በሚመለከት ከማንኛውም ሰውና ቦታ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ብቁ የሆኑትን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በማቅረብ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያደርጋል፡፡

፪/ በየደረጃው ለሚገኙ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንትነትና ምክትል ፕሬዝዳንትነት የተመለመሉ እጩዎችን በሚመለከት ከማንኛውም ሰውና ቦታ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ብቁ የሆኑትን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በማቅረብ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያደርጋል፡፡

፫/ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የመለመላቸውን የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞችን በሚመለከት ከማንኛውም ሰውና ቦታ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ብቁ የሆኑትን በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያደርጋል፡፡

፬/ በፌደራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሬጅስትራሮችንና ረዳት ዳኞችን ይሾማል ደሞዝ፣ አበላቸውን፣ ጥቅማጥቅሞቻቸውንና ከስራ የሚሰናበቱበትን ሁኔታ ይወስናል፡፡

24. Powers and Functions of the Council

The Council shall have the following powers and duties:

1/ It shall collect evidence from any person or source regarding candidates recruited for the presidency and vice-presidency of the Federal Supreme Sharia Court; and to submit qualified candidates to the President of the Federal Supreme Court for appointment by the House of Peoples' Representatives.

2/ shall collect relevant evidence from any person or source, assess their qualifications of candidates recruited for the offices of President and Vice-President of the remaining Federal Sharia Courts, and submit those found qualified to the President of the Federal Supreme Court as applicable for nomination and appointment by the House of Peoples' Representatives.

3/ In collaboration with the Council of Ulamas of the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council, it shall collect evidence from any person or source regarding recruited Sharia Court judges and to submit qualified candidates to the House of Peoples' Representatives for appointment upon the recommendation of the President of the Federal Supreme Sharia Court.

4/ It determines the appointment of registrars and assistant judges of Federal Sharia Courts upon the recommendation of the President of the Federal Supreme Sharia Court and to determine their salaries, allowances, benefits, and conditions of dismissal.

፭/ የጉባዔውን አደረጃጀትና አሰራር መመሪያና የጉባዔው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የሚመሩበትን የስራ ደንብ ያወጣል፡፡ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡

5/ It shall issue Directives for the organization and procedure of the Council and the working Regulations for its various committees; and to oversee their implementation.

፮/ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የወል የዳኝነት ስልጣን ስር በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የተጠቃለሉ የሸሪዓ መሰረታዊና የስነ ስርዓት ህግ ማጣቀሻ ያዘጋጃል፡፡ ያጸድቃል፡፡

6/ In collaboration with the Council of Ulamas, it shall prepare and approve consolidated reference codes of substantive and procedural Sharia laws for matters falling under the common jurisdiction of Sharia Courts.

፯/ የዳኞች ምልመላ፣ ስነምግባር ምዘና እና የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ ስነስርዓት ደንብና መመሪያ ያወጣል፡፡ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

7/ It shall issue Regulations and Directives on the recruitment, ethical evaluation, and disciplinary procedures of judges; and to oversee their implementation.

፰/ ተፈጻሚነት ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ሰራተኞችን የሚመለከቱ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው የፍርድ ቤቶቹን እሴት መሰረት ያደረገ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰራተኞች የአሰራር ስነ ስርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

8/ Without prejudice to the applicable laws governing the administrative personnel of the Federal Courts, it shall issue a Code of Conduct and Administrative Procedure Directives for the employees of the Sharia Courts, founded upon and reflecting the values of the Courts.

፱/ የጉባዔው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የስራ አፈጻጸምን ይገመግማል፣ በግምገማው መሰረትም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

9/ It shall evaluate the performance of various committees of the Council and render decisions based on such evaluations.

፲/ የፌዴራል ጠቅላይ፣ ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች እንዲሁም በማንኛውም የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች ላይ የሚቀርቡ የስነምግባር ጥሰት ክስ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

10/ It shall investigate and rule on allegations of ethical misconduct brought against the Presidents and Vice-Presidents of the Federal Supreme, Federal High, and Federal First Instance Sharia Courts, as well as against judges serving in any Federal Sharia Court.

፲፩/ በወንጀል የተጠረጠሩ ዳኞችን ያለመከሰስ መብት ያነሳል፡፡

11/ It shall lift the immunity of judges suspected of committing a crime.

፲፪ ለፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በስነስርዓት ህግና ሌሎች የመደበኛ ትምህርት ርዕሶች ላይ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

12/ It will ensure that Federal Sharia Court judges receive continuous training on procedural laws and other formal educational topics.

፲፫/ የዳኞችን እድገት፣ ደሞዝ፣ አበል፣ እረፍት ህክምና እና ሌሎችም ጥቅማጥቅሞችን ይወስናል፡፡

፲፬/ ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች መንግስት ከሚሰጠው በጀት በተጨማሪ ለጉባዔው ተጨማሪ የበጀት ምንጭ ያፈላልጋል፡፡

፲፭/ ለጉባዔው አባላት የሚከፈለውን አበል ይወስናል፡፡

፲፮/ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የሸሪዓ ህግ ጥናት፣ ምርምርና ማሰልጠኛ ማዕከል ለማቋቋም ይሰራል፡፡

13/ It shall determine the promotion, salary, allowances, leave, medical benefits, and other perks of judges.

14/ It shall seek additional budgetary sources for the Council beyond the budget allocated by the government to Federal Sharia Courts.

15/ It shall determine the allowances payable to the members of the Council.

16/ To work towards the establishment of a Sharia Law study, research, and training center in collaboration with the Council of Ulamas of the Ethiopian Islamic Afairs Supreme Council.

፳፭. <u>የጉባዔው ስብሰባና አሰራር</u>

፩/ ጉባዔው ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ በመደበኛነት ይሰበሰባል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ ከጉባዔው አባላት ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፭) ወይም ጉባዔው በሚያወጣው የስብሰባ አመራር ሥነሥርዓት ደንብ በልዩ ሁኔታ ድምጽ እንዲሰጥባቸው የተወሰኑት እንደተጠበቁ ሆነው የጉባዔው አባላት በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡ ሆኖም ግን ድምጹ እኩል ለእኩል በሚሆንበት ጊዜ የዕለቱ የጉባዔ ሰብሳቢ ድምጽ መለያው ይሆናል፡፡

፬/ ማንኛውም የጉባዔው አባል የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት እንደሆነ ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በጉባዔውም ሆነ በኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

፭/ የጉባዔው አባላት የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማንኛውም ግለሰብ በውክልና መስጠት አይችሉም፡፡

25. <u>The Council's Meetings and Procedure</u>

1/ The Council shall meet regularly at least once a month. It may also be convened at any time it deemed necessary.

2/ A quorum of the Council shall be constituted when at least two-thirds of its members are present.

3/ Decisions of the Council shall be made by a majority vote of the members, provided that the special voting requirements set out under this Proclamation Article 18 Sub-Article (5) or any rules of procedure adopted by the Council are met. In the case of a tie vote, the presiding officer of the meeting shall have a casting vote.

4/ Any member of the Council who is under disciplinary proceedings shall not participate in Council or committee meetings until a final decision is rendered.

5/ Subject to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, members of the Council shall not delegate the powers and functions conferred upon them to any person by proxy.

፮/ ከዚህ በላይ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ አመራር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፳፮. <u>የጉባዔው ጽሕፈት ቤትና ሰራተኞች</u>

፩/ ጉባዔው የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።

፪/ ጽሕፈት ቤቱ ጉባዔው በሚያወጣው መስፈርት መሰረት በጉባዔው የሚሾም ኃላፊ ይኖረዋል።

፫/ የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል።

፬/ የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፦

ሀ) ከጉባዔው ሰብሳቢ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የጉባዔውን ስብሰባ አጀንዳዎች ከጉባዔው ሰብሳቢ ጋር በመሆን በማዘጋጀት ከጉባዔው ስብሰባ ቀን ሶስት ቀናት በፊት ለጉባዔው አባላት እንዲደርስ ያደርጋል፤

ለ) በጉባዔው ስብሰባዎች ላይ በጸሐፊነት በመገኘት ቃለ ጉባዔ በመያዝ ቃለጉባዔዎች በአባላቱ መፈረማቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) የጉባዔውን ጽሕፈት ቤት የየእለቱን ስራ በኃላፊነት ይመራል ይቆጣጠራል፤

መ) ለጉባዔው የስራ ክፍሎችና ኮሚቴዎች እንደአስፈላጊነቱ ቢሮዎችን ያደራጃል፤

ሠ) ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይቀጥራል የስራ አፈጻጸማቸውን ይገመግማል በግምገማው መሰረትም ውሳኔ ይሰጣል፤

ረ) የጉባዔው አባላትን አበል ይከፍላል፤

ሰ) የጉባዔውን የስራ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ወይም በጉባዔው በተጠየቀበት ወቅት አዘጋጅቶ ያቀርባል።

6/ The Council may issue its own rules of procedure for meetings, provided these are consistent with the provisions set forth above.

26. <u>Secretariat and Staff of the Council</u>

1/ The Council shall have its own Secretariat.

2/ The Secretariat shall be led by a Chief Secretary appointed by the Council in accordance with criteria issued by it.

3/ The Secretariat shall employ the necessary staff required for its operations.

4/ The Head of the Council's Secretariat shall:

a) In accordance with the direction provided by the Chairperson of the Council, jointly prepare the agendas for the Council's meetings and ensure their distribution to the members at least three days prior to the meeting date;

b) Attend the meetings of the Council in the capacity of Secretary, record minutes, and ensure that such minutes are duly signed by the members;

c) Direct and oversee the day-to-day operations of the Council's Secretariat;

d) Organize offices for the various departments and committees of the Council as may be necessary;

e) Recruit personnel essential for the operations of the Secretariat, evaluate their performance, and render decisions based on such evaluations;

f) Effect payment of allowances to the members of the Council;

g) Prepare and submit performance reports of the Council on a quarterly basis or whenever requested by the Council.

፳፯. የጉባዔው በጀት

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደልተራ (ረ) እና (በ) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጉባዔው በጀት ከፌዴራሉ መንግሥት በሚሰጥ በጀትና ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ድጋፍ ይሸፈናል።

ክፍል ስምንት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፰. ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎች

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልላቸውን መሠረት አድርገው የቀረበላቸውን ጉዳዮች ሲመረምሩ የሸሪዓውን ሕግ መሠረት አድርገው ይዳኛሉ።

፪/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚዳኟቸውን ጉዳዮች የሚመሩት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ንዑስ አንቀጽ(፮) ስር በተደነገገው መሰረት በሚዘጋጀው የተጠቃለለ የሸሪዓ ስነ ስርዓት ህጎች መድብል መሰረት ይሆናል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠቃለለ የሸሪዓ ስነ ስርዓት ህግ እስኪዘጋጅ እንዲሁም በሸሪዓ ስነ ስርዓት ህጉ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤቶቹ የመደበኛውን የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ተከትለው ይሰራሉ።

፳፱.ፍርድ ቤትን ስለመድፈር

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቱን ወይም የዳኞችን በነጻነት መስራት የሚጋፋ ወይም በዳኞች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ወይም ለማድረግ የሞከረ ማንኛውም ሰው እንደ ነገሩ ከባድነት ከሶስት ወር ባላነሰ ቀላል እስራት ወይም ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት ወይም ከ፲ ሺህ ብር (አስር ሺህ ብር) ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

27. Budget of the Council

Without Prejudice to Article 19 Sub-Article (2) paragraph (f) and (j) of this Proclamation, the budget of the Federal Sharia Courts Administration Council shall be covered by allocations from the federal government and other sources.

PART EIGHT

Miscellaneous Provisions

28. Applicable Laws

1/ When Federal Sharia Courts adjudicate cases brought before them within their jurisdiction, they shall render decisions based on Sharia law.

2/ The issues adjudicated by the Federal Sharia Courts shall be governed by the codified compilation of sharia rules of procedure to be prepared in accordance with the framework set out under Article 24 Sub-Article (6) of this Proclamation.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the Courts shall apply the regular Civil Procedure Code pending the preparation of a consolidated Sharia Procedure Law, as well as for matters not covered by Sharia procedural law.

29. Contempt of Court

1/ Any person who interferes with the independence of the Federal Sharia Courts or of the judges, or who exerts or attempts to exert influence upon the judges, shall, depending on the gravity of the offence, be punishable with simple imprisonment for a term of not less than three months, or rigorous imprisonment for a term not exceeding two years, or a fine not exceeding Ten Thousand Birr (Birr10,000).

ይህንንም ችሎቱ በያዘው መዝገብ ላይ ውሳኔውን ያሳርፋል።

፪/ የችሎቱን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ መፈጸም ሲገባው ያልፈጸመ ወይም እንዳይፈጸም መሰናክል የፈጠረ ወይም ያልተባበረ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ፭ ሺህ ብር (አምስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

2/ Any person who, being under a duty to execute an order or decision of the Court fails to do so or creates an obstacle to its execution or fails to cooperate in its execution shall be punishable with simple imprisonment for a term not exceeding two years or a fine not exceeding Birr Five Thousand (Birr 5,000).

፴. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔዎችና ትዕዛዞች

30. Decisions and Orders of Federal Sharia Courts

፩/ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሥልጣን ክልላቸው በሚሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸውን ውሳኔዎችና ትዕዛዞች አስፈጻሚ ክፍሎች እንዲፈጽሙ ለማዘዝ ይችላሉ።

1/ Federal Sharia Courts at all levels shall have the power to order the executive organs to execute decisions and orders rendered within their jurisdiction.

፪/ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ትዕዛዝና ውሳኔ የደረሳቸው አስፈጻሚ አካላትም ሆኑ ግለሰቦች በትዕዛዙ መሠረት የመፈጸምም ሆነ የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው።

2/ Any executive organ or individual to whom the orders and decisions of Sharia Courts are directed shall have the obligation to comply with or ensure the execution of such orders.

፫/ የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ መሰረት ለማስፈጸም፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉና ሌሎች የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ፍርዶች አስፈጻሚ አካላት ህግና መመሪያዎች መሰረት አስፈላጊውን ህጋዊ የአፈጻጸም እርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ።

3/ For the purpose of executing court decisions, Federal Sharia Court judges may take necessary legal execution measures in accordance with the Civil Procedure Code and other laws and Directives governing the executive organs of regular court judgments.

፬/ በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይንና ትዕዛዝ የሰጠባቸው ጉዳዮች ህጋዊ በመሆናቸው ስነ ስርዓቱን መድገም ሳያስፈልግ የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ ተግባራትን እንዲያከናውን ስልጣን በተሰጠው የፌዴራል ወይም የክልል አካል እውቅና ይሰጣቸዋል።

4/ Judgments, decisions, rulings, and orders rendered by the Federal Sharia Courts shall by virtue of their legal validity be recognized by the competent Federal or Regional authority empowered to authenticate and register documents without requiring the underlying proceedings to be repeated.

ሯ/ የፍርድ ቤቶቹን ትዕዛዞችና ውሳኔዎች ትክክለኛ ግልባጭ የሚያረጋግጡ ሬጅስትራሮች የፊርማ ናሙና የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሬጅስትራሮች ፊርማ ናሙናዎች ወደሚላኩባቸው የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት መላካቸውን ፍርድ ቤቶቹ ያረጋግጣሉ።

፴፩. <u>ስለዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰን</u>

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ የፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች እንዲሁም ዳኞች ላይ የሚቀርብ ዲሲፕሊን ክስ መርምሮ የመወሰንና በውሳኔው መሰረት መፈጸሙን የመከታተል ስልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል።

፪/ ከዚህ ጋር ተያይዞ ጉባዔው የሚያወጣቸው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞችና ሰራተኞች አሰራር ስነስርዓትን የሚመለከቱ መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኝነት አስተዳደር አዋጅ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች መተዳደሪያ ደንብና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሰራተኞች ደንብ እንደአግባብነታቸው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞችንና ሰራተኞች ለሚመለከቱ የዲሲፕሊን ጉዳዮች አወሳሰን ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

፴፪. <u>መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

፩/ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ቀርበው በመታየት ላይ ያሉና የነበሩ ጉዳዮች ቀደም ሲል ሲታዩበት በነበረው አግባብ መታየታቸውን የሚቀጥሉ ይሆናል።

5/ The Courts shall ensure that the specimen signatures of registrars who certify true copies of court orders and decisions are transmitted to the domestic and international institutions to which the specimen signatures of regular court registrars are sent.

31. <u>Disciplinary Measures Procedure</u>

1/ The Council shall have the power and duty to investigate and determine disciplinary charges brought against the Presidents, Vice-Presidents, and judges of the Federal Sharia Courts, and to oversee the implementation of its decisions.

2/ Without prejudice to the Directives issued by the Council governing the code of conduct of Federal Sharia Court judges and employees, the Federal Courts Proclamation, the Federal Judges Administration Regulation and the Federal Courts Administrative Employees Regulation shall as appropriate apply to the determination of disciplinary matters relating to Federal Sharia Court judges and employees.

32. <u>Transitional Provisions</u>

1/ Any matter pending or adjudicated before the Federal Sharia Courts at or before the time this Proclamation enters into force shall continue to be heard and determined in accordance with the Proclamation they are filed under.

፪/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተደራጅቶ ወደ ስራ እስከሚገባበት ጊዜ ድረስ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በባለጉዳዮች ጠያቂነት በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ወይም በችሎቶቹ መካከል መሰረታዊ የትርጉም ልዩነት ያለባቸው የሸሪዓውን ህግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲነሱ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው እንዲያዩት ለማድረግ ይችላል።

፴፫. <u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በጀት</u>

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡-

ሀ) ከፌዴራሉ መንግሥት በሚመደብ በጀት፤

ለ) ከሌሎች ጉባዔው ካጸደቃቸው ምንጮች ከሚገኝ ድጋፍ።

፪/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የበጀት አሰባሰባቸውና አጠቃቀማቸው የፌዴራል የመንግስት ፋይናንስ፣ ግዢና ንብረት አስተዳደር እንዲሁም የኦዲት ህጎችን መሰረት አድርገው ይሰራሉ።

፴፬. <u>ስለ ዳኝነት ክፍያ</u>

በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ጉዳዮች የዳኝነት ክፍያን በሚመለከት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አከፋፈል ደንብ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

፴፭. <u>ስለተሻሩ ህጎች</u>

፩/ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፷/፲፱፺፪ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማንኛውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

2/ Until the Cassation Bench of the Federal Supreme Sharia Court is established and commences operation, the President of the Federal Supreme Sharia Court may upon the application of a party constitute a Bench of not fewer than five judges to hear any matter involving a fundamental divergence in the interpretation of Sharia law among the Federal Sharia Courts or their Benches.

33. <u>Budget of the Federal Sharia Courts</u>

1/ The Federal Sharia Courts shall be financed from the following sources:

a) Allocations from the Federal Government budget;

b) Additional support from other sources subject to the abroval of the council.

2/ The Federal Sharia Courts shall administer the collection and utilization of their budget in accordance with the Federal laws governing public finance, procurement and property administration, and auditing.

34. <u>Court Fees</u>

Court fees payable in respect of matters brought before the Federal Sharia Courts shall be assessed and collected in accordance with the provisions of the Federal Courts Fees Regulation.

35. <u>Repealed Laws</u>

1/ Proclamation No.188/2000, which was issued to strengthen the structure of the Federal Sharia Courts, is hereby repealed.

2/ Any law that contradicts or governs matters covered under this Proclamation shall have no legal force or effect.

፴፮. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

ታዬ አፅቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

36. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 10th day of August 2026

TAYE ATSKESELASSIE
PRESIDENT OF THE FEDRAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA